
የሥርዓተ-ፆታ ፍትህ ፖሊሲ
የሉተራ
ዓለም
ፌዴሬሽን

# የፆታ ፍትህ ፖሊሲ

# የዓለም ሉተራን ፌዴሬሽን

## ማውጫ


መቅድም ....................................3

በፆታ ፍትህ መንገድ አብሮ መጓዝ፡ ትምህርታዊ ጉዞ.............................4

1. የፆታ ፍትህ ፖሊሲ መመሪዎች ...............................5

2. **የፆታ ፍትህ ፖሊሲ እቅድ** ....5

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እና መሠረታዊ ምክንያት.......................6

ፍቺ.........................................9

የፆታ ፍትህ፡ የህብረቱ ራዕይ.............9

መስፈርት .................................10

ግብ.......................................10

ዓለማ፡ የፆታ ፍትህ ፖሊሲ ለምን አስፈለገ? .................................10

ለዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ፖሊሲ ምንድነዉ?...............................11

የካዉንስል ዉሳኔዎች ...................11

የሃላፊነት ደረጃዎች .....................12

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲ መመሪያዎች .....................13

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ፆታ ፍትህ እቅድ......................................14

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ህብረት ወደ አካታች በሚደረገዉ ጉዞ የት ነዉ **የሚቆመዉ**?...........................15

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ወደ ፆታ ፍትህ ጉዞ .................................17

መጽሐፍ ቅዱሳዊና ስነ መለኮታዊ መሠረት፡ የፆታ ፍትህ ለሉትራዊያን ለምን አስፈላጊ ሆነ? .....................18

ቅዱሳት መጻሕፍት፡.....................19

ጽድቅና ፀጋ፡ ነፃነትና ክብር ለሁሉም የሰው ዘር .................................21

የእግዚአብሔር እንደ ሰዉ ሥጋ መልበስ፡ .................................23

አርአያና ፍትህ ..........................23

ቅዱሳት ሚስጥራት፡ ....................24

የቤተክርስቲያን ምሦሦዎች፡............26

መሪነት መጋራትና የእኩልነት ደቀ መዝሙርነት..............................26

እቅዱን በአውድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መመሪያዎች...................27

ቁጥጥርና ተጠያቂነት፡ ..................27

የስነ-ፆታ ትንተና፡ ........................28

አሳታፊነት.................................29

አቋራጭ የፆታ ፍትህ ....................29

ችሎታን ማሳደግ.........................30

በፆታ ፍትህ አመለካከት የአቂም ግንባታ እቅድ፡ .....................................30

ድርጅታዊ አደረጃጀቶች.................31

ደህንነትና ማስፈንና ህብረትን መፈወስ ............................................32

የወል ተጠያቂነትን ለመወጣት የምያግዙ የአሰራር ዘዴዎች .........................34

መፍትሔ ቃላት...........................35

## መቅድም

ፍትህን ለማስከበር የሚቀርበው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥሪ የኅብረቱ ማንነትን የመረዳት ዋና አካል ነው፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ነጻ ያወጣናል፤ በክርስቶስ ባለን እምነት ወደ አንድነት የሚያመጣን እና ለፍትህ፣ ለሠላም እና ለእርቅ አብረን እንድንኖር እና እንዲንሠራ ያደርገናል፡፡

የዓለም ሉትራን ፌድሬሽን (LWF) ሴቶች እና ወንዶች በቤተ ክርስቲያን እና በህብረተሰብ ዉስጥ እኩል ተሳታፊዎች እንዲሆኑ፣ በውሳኔዎቹ፣ በሚሰሩት ስራዎች እና ፕሮግራሞች ውስጥም ሴቶችን በመካተት እና በማገዝ ተግቶ እየሰራ ነው፡፡ የዓለም ሉተራን ፌደሬሽን ታሪክ ሲመረመር የተወሰኑት ውሳኔዎቹ እና ድርጊቶቹ ሲታዩ ይህንን ትጋት ያሳያሉ፡፡

የዓለም ሉትራን ፌድሬሽን (LWF) በ2013 እ.ኤ.አ. ያፀደቀው የጾታ ፍትህ ፖሊሲ ህብረቱ ወደ አካታችነት የሚያደርገውን ጉዞ የሚያግዝ ጠቃሚ መሣሪያ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ፖሊሲ አባል አብያተ ክርስቲያናትን ያሳተፈ እና የእነርሱን ልምድ ያካተተ፣ በሉተራዊ ማንነት ላይ የታነጸ፤ ሉተራዊ አስተምህሮ እና መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ ሲሆን በህብረቱ ሥራ ውስጥ ጾታዊ ተሳትፎ ቀዳሚ ትኩረት እንዲያገኝ በስልቶች እና በዕቅዶች ውስጥ እንዴት በአውዱ በተግባር ላይ



*ቄስ ማርቲን ጀንግ*
*የዓለም ሉትራን ፌድሬሼን*
*(LWF) ጠቅላይ ፀሐፊ*
*© LWF/H. Putsman-Penet*

ማዋል እንደምችል አስፈላጊውን መመሪያ እና ዘዴዎችን ይሰጣል፡፡ የዓለም ሉትራን ፌድሬሽን (LWF) የሴቶችን ጥቃት ለመመከት እና ሴቶች በአመራር ተሳታፊዎች እንድሆኑ ለማረጋገጥ እና የፌደሬሽኑ የአካታችነት ራዕዩን ለመተግበር የፆታ ፍትህ ፖሊሲ ታሪካዊ ወሳኝ ድርግት ነው፡፡

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተካተቱት ዝርዝር ጉዳዮች ለግንኙነት እና ለመዋቅር ለውጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ለመሳተፍ መንገድ ከፋቾች ናቸው፡፡ ይህ ለሁሉም የሚደረግ ጥሪ ሲሆን በተለይም ለቤተ ክርስቲያ መሪዎች፣ ለሥነ - መለኮት ሊህቃን፤ በተለያዩ የአመራር እና ውሳኔ ሰጪ ሥፍራዎች ላሉ ሴቶች እና ወንዶች፣ እንዲሁም ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን በመምራት ላይ ያሉ ሁሉ የፆታ ፍትህ ጉዳይ የእምነት ጉዳይ መሆኑን እንዲያረጋግጡ የተደረገ ጥሪ ነው፡፡ በመሆኑም የፆታ ፍትህ የቤተክርስቲያንን ትክክለኛ ማንነት እና ቤተክርቲያን በማህበረሰብ ውስጥ የትንቢት ድምጽ ያላት መሆኗን ያመለክታል፡፡

የፆታ ፍትህ ፖሊሲ ወደ እናንተ የደረሰው በሴቶች ላይ እየደረሰ ያለው ተግዳሮት በቤተክርስቲያንም ሆነ በህብረተሰብ ውስጥ በቀጠለበት በዚህ ወቅት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ እንዲሁም በሴቶች እና በወንዶች መካከል ያለው ግንኙነት በፍትህ ላይ እንዲመሰረት እግዚአብሐየር ጥሪ ባለበት ወቅት ነው፡፡ ይህ ፖሊሲ የታተመው የዓለም ሉትራን ፌዴረሽን ህብረቱ የተሐድሶ ቀጣይነትን በሰማበት ((semper reformanda) እና 500ኛ የሉትራን ቤተክርስቲያን ተሐዲሶ በ2017 ለማክበር በምዘጋጅበት ጊዜ ነው፡፡ ይህን ስታነቡና ስታጠኑ በቤተክርስቲያን መዋቅርና ሕይወት እንዲታይ በጸሎት እና ነገሮችን በመለየት እንዲሆን አመክራለሁ፡፡

ምክንያቱም ፆታን በተመለከተ በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባ ግንኙነት ተገቢ እና ትክክለኛ እንዲሆን በቁጥጥሩ ሥር ባለው በእግዚአብሔር ኃይል አማካኝነት ሊለወጥ ይገባል፡፡

*ቄስ ማርቲን ጀንግ*
*የዓለም ሉትራን ፌድሬሼን*
*(LWF) ጠቅላይ ፀሐፊ*
*© LWF/H. Putsman-Penet*



## በፆታ ፍትህ መንገድ አብሮ መጓዝ፡ ትምህርታዊ ጉዞ

ለራስሽ የመንገድ ምልክት አድርጊ፣ መንገድንም የሚመሩ ዓምዶችን ትከይ፣ ልብስሽንም ወደ ሄድሽበት መንገድ ወደ ጥርግያው አቅኚ፣ አንቺ የእስራኤል ድንግል ሆይ፣ተመለሺ፣ወደ እነዚህም ወደ ከተሞችሽ ተመለሺ፡፡(እር 31፡21) በዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ኅብረት የፆታ ፍትህ ትምህርታዊ ውይይት እንዴት ማስተማር፣ መማር፣ እርስ በርሳችን በመተጋገዝ መሄድ እንዳለብን የሚያበረክተዉ አስተዋጽኦ ሰፊ ነዉ፡፡

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፣ የእግዚአብሔር ሕግ ፍጽም ነዉ፣ ነፍስን ይመልሳል፣ የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነዉ፣ ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል፡፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነዉ፤ ልብንም ደስ ያሰኛል፤ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ብሩህ ነዉ፣ ይህንንም ያበራል፡፡ የእግዚአብሔር ፍርሃት ንጹህ ነዉ፣ ለዘላለም ይኖራል፣ የእግዚአብሔር ፍርድ እዉነትና ቅንነት በአንድነት ነዉ፡፡ ከወርቅና ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል፤ ከማርና ወለላም ይጣፍጣል፡፡(መዝ. 19፡7-10)

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሕግ ፍጹምና ነፍስን የሚመልስ ነው፡፡ እናም ልብን በማስደሰት ሴቶችና ወንዶችን ፍትህንና በመካከላቸው በሚኖረው ግንኙነት ታማኞች እንዲሆኑ ይረዳል፡፡

ይህ ዶኩመንት በሁለት ይከፈላል፡ አንደኛው የጾታ ፍትህ ፖሊሲ መመሪያ ሲሆን ይህም መመሪያ የጾታ ፍትህን በሁሉም የህብረቱ መዋቅሮች እንዴት በሥራ ላይ እንደምናውል ያስተምረናል፡፡

## 1. የፆታ ፍትህ ፖሊሲ መመሪያዎች

አስርቱ መመሪያዎች የዓለም ሉትራን ፌድርሽን ህብረት የፆታ ፍትህን በማረጋገጥ ረገድ ማዕከላዊ ናቸው፡፡ እነርሱ የፆታ ፍትህ ምንነት ለህብረቱ ምን ማለት እንደሆነ የሚገልጹ፣ ህብረቱ ወደ ፆታ ፍትህበሚያደርግ ጉዞ መመሪያ የሚሰጡ ናቸው፡፡

## 2. የፆታ ፍትህ ፖሊሲ እቅድ

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የጾታ ፍትህ ፖሊሲ እቅድ የፆታ ፍትህ መመሪያዎችን በቤተክርስቲን አባላት በአውዳቸው ተግባራዊ የሚደርጉበት መሳሪያ ነው፡፡ ሂደቱ በየአውዱ ተቆጣጣሪ ይኖረዋል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ጠቅላይ ፀሐፊ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲ ተግባራዊነት ለፌዴሬሽኑ ካውንስል ሪፖርት ያደርጋል፡፡ ፕሮግራሞቹ እና አጠቃላይ ሂደቶቹ ለህብረቱ አባል አብያተ ክርስቲያናት በቀላሉ የሚደርሱለት እና የራሳቸው የምያደርጉበት ዘዴዎችና መንገዶቹ (መሳሪያዎቹ) ይዘጋጃል፡፡

ግቡ እዉቀትን ማካፈል እና እርስ በርስ መደጋገፍን ተግባራዊ ለማድረግ የትምህርት ሁኔታን ማመቻቸት ይሆናል፡፡

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እና መሠረታዊ ምክንያት

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ምድርም ባዶ ነበረች፣ አንዳችም አልነበራትም፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በዉሃ ላይ ሰፍፎ ነበር። ...... እግዚአብሔርም ያደረገዉን ሁሉ አየ፣ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ። (ዘፍ 1፡1-2፣ 31ሀ).

በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ፣ የፍጥረት ታርክ ሁሉም ፍጥረታት በእግዚአብሔር ላይ እንደተደገፉ ያሳያል።

በዘፍጥረት 2 ውስጥ የምናየው የፍጥረት ታሪክ ሰው ብቻ በተቃራኒ (ወንድና ሴት) የተገለጸ ሳይሆን አንዱ የሰው ፆታ (ወንድ) በሴት ላይ የበላይነት እንዳለውም ጭምር ነው።

እንዲሁም የፍጥረት ታሪክ በጣም አስፈላጊው የልዩነት ሀሳብ በእግዚአብሔርና በፍጥረታት፣ በወንድና በሴት መካከል ብቻ እንዳይደለ ይገልጻል። ፍጥረት በእግዚአብሔር ላይ ይደገፋል፤ ይህ ፍጥረትን በተመለከተ የመጀመሪያ ስነ-መለኮታዊ ግንኙነት ነው።

ይህ የእግዚአብሔርና የፍጥረት ልዩነት በፍቅር እንጂ በሰዎች መካከል ያለውን የፆታ ልዩነትን በእኩልነት ማካተት አይደለም።

ሌላው አስፈላጊ ነጥብ እኩልነት ነው (ዘፍ 1፡27)። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በእኩልነት እንደ ፈጠረ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ሰው ፍጥረታትን እንዲጠብቅና እንድንከባከብ ትዕዛዝ ሰጠው። ከዘፍጥረት መጽሐፍ እንደምናነበው የጥበቃና ፍቅር ስነ ምግባር የፆታ ፍትህ ስነ ምግባርን ይገልጻል።የሰው ዘር በአንድነት ለእርስ በርስና ለፍጥረታት በሙሉ መጋቢያን እንዲሆኑ ተጠርተዋል።

እግዚአብሔርም አለ። ሰዉን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፣ የባህር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መልክፈጠረው፣ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸዉ። (ዘፍ 1፡26-27). ቅዱሳን መጻሕፍት ለሁለቱም ፆታዎች መጠቃለል መሠረት ይሆናል። ከወንገላት እንደምናነበው፣ ኢየሱስ ሴቶችን እንዴትና በምን መንገድ ተቀባይነታቸውን እንዳሳየ እናያለን። ይህም በፍቅር፣ በመቀበልና ከወንዶች ጋር እንዳስተናገዳቸው እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምስክርነቶች የሚያረጋግጡት የእግዚአብሔር ቃል የተትረፈረፈ ሕይወት እንደሚሰጥ፣ ይህም ደግሞ ለሁሉም እንደሆነ፣ ለወንዶችም ለሴቶችም እንደ ሆነ ያሳያል። ከመጽሐፍ ቅዱሳችን እንደምናነበው ቤተክርስቲያን በጥምቀት የሁሉም እኩልነት ያለባት እንደሆነ እናነባለን። ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ

ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሰችኋልና፡፡
አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፣ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰዉ ናችሁና፡፡ (ገላ 3፡ 27-28).
አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን፣ እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና፡፡ ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል፡፡ (1ቆሮ 12፡13) በፆታ መካከል ያለውን ግንኙነት በምናነሳበት ጊዜ እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች ኃብረቱ ለአንድነት አንድነሳሱ ያደርጋል፡፡ በሴቶች ላይ ያለውን ጭቆናና ጫና በመሰበር በወንዶችና በሴቶች መካከል ሙሉ አብሮነትና እኩልነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡



## ኃላፊነት

በጥቅምት 2009 የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ጉባኤ አንድ ዶኩመንት ተቀብሎ ነበር:: ዶክመንቱም እንዲህ የሚል ነበር፣ በእናንተ መካከል አየሆንም፣ በፆታ ላይ የተመሰረተ እምነትና ሃይል፣ የቤተክርስቲያን አባላት በክትትል ሂደት ዉስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ለማበረታታትና የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲ ግንባታ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ስለዚህ በ2010 የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን አስራ አንደኛ ጉባኤ ሁለት ዉሳኔዎችን አስተላለፈ::

## 1. የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን አካታችነት፡

### የፆታ ሚዛናዊነት፡

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ጉባኤ ባለስልጣናትና ሌሎች ኮሚቴዎች በሙሉ፣ እንዲሁም ሌሎች ጊዜያዊ ኮሚቴዎች፣ አርባ በመቶ ሴቶችና አርባ በመቶ ወንዶች እንዲካተቱ ተደረገ:: ይህም ኮታዎችን በእኩልነት ተግባራዊ ለማድረግ ታስቦ ነው::

በማንኛውም ሥራ ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን የዓለም ሉትራን ፌደረሽን ይደግፋል፣ ያከብራልም::

## የፆታ ፍትህ ውሳኔ

አባል አብያተክርስቲያት የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲን በአጥጋቢ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማድረግ ጉባኤ እንጠራለን::

በዚህም ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በቤተክርስቲያን ህይወትና በዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ማህበረሰብ፣ እንዲሁም በህብረተሰብ ዉስጥ የላቀ እንዲሆን ነው::

የሴቶች በሥልጣን ውስጥ፣ ተሳትፎአቸውን ለማረጋገጥ ትክክለኛ ህግና መመሪያ ፖሊሲን እንዲያዘጋጁ አባል ቤተክርስቲናትንን እንጠራለን:: የሴቶች በቅስናና በስለ - መለኮት ትምህርት ሙሉ ተሳታፊነትንም እንዲያረጋግጡ እናደርጋለን::

በአባል አብያተክርስቲያናት ህይወት ውስጥ እንደ ስነ-መለኮትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ የስነ-ፆታ ትንተናን እንዲያጠቃልሉ አባል አብያተ ክርስቲያናትንና የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ጠቅላይ ፀሐፊን እንጠራለን:: በሁሉም ደረጃ ተግባራዊ የሚሆን አውዱን የጠበቀ የስነ-ፆታ ፖሊሲ ግልጽ እቅድ እንዲያዘጋጁ እንጠይቃለን::

ጉባኤውን የምንጠራው እንደዚህ አይነቱን መመሪያ ለማዘጋጀትና ለማሻሻል ነው፡፡

ግጭትን ለመቃወምና የሁሉም ሰው መብት እውቅና እንዲኖረው የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽንና አባል አብያተክርስቲያናቱን እንጠራለን፡፡ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሼን ጉባኤ የፆታ ፍትህ በአጀንዳው ውስጥ በቋሚነት እንዲኖረው እንጠይቃለን፡፡

ምክንያቱም በወጣት ወንዶችና በወጣት ሴቶች መካከል የተስተካከለ ሚዛን ስለለለ ይህ ጉባኤ የተለየ ትኩረት እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡

በቦጎታ ኮሎምቢያ በ2012 የተሰበሰበው የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ጉባኤ ህብረቱ ቢሮ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲ ረቂቅ በ2013 እንዲያቀርብ ጠየቀ፡፡ በመሆኑም የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲ በጄኔቫ በተደረገዉ በ2013 ስብሰባ ተዘጋጀ፡፡

## ፍቺ

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ደግሞም ለህብረቱ የፆታ ፍትህ መሠረት ይጥላል፡፡

የፆታ ፍትህ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩትንና የፍጥረታት ባለአደራ የሁኑትን የሴቶችና የወንዶች እኩልነትን ይጠብቃል፡፡ የፆታ ፍትህ የሚገለጸዉ ሚዛኑን በጠበቀ የወንዶችና የሴቶች እኩልነት ዉስጥ ነዉ፡፡

## የፆታ ፍትህ፡ የህብረቱ ራዕይ

በእግዚአብሔር ፀጋ ነጻ በመዉጣት የህብረቱ በክርስቶስ ዉስጥ መኖርና ለፍትህ፣ ለሠላምና ዓለምን ለማስታረቅ አብሮ መስራት፡፡



ህብረቱ በክርስቶስ ለመኖር፣ ፍትህ ማጣትንና ጭቆናን ለማስቀረት እንዲሰራ ተጠርተዋል:: በህብረት ዉስጥ መሆን በእግዚአብሔር ወንጌል ፀጋ መንፈሳዊ ጉዞን ለመጋራት፣ በጥምቀትና በቅዱስ ቁርባን ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ጋር እንድ መሆን ነዉ::

በክርስቶስ መሆን የሚያመለክተዉ ምንም እንኳ ልዩነታችን ቋሚ ቢሆንም ልዩነታችን ስጦታችን፣ አንዱ ከሌላዉ የማይበልጥ መሆኑን ያሳያል:: ልዩነት እኩል አለመሆን አይደለም:: ፍትህ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ በትንቢታዊና በስነ-መለኮታዊ ቋንቋ ይጠራል::

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲ፣ መመሪያዎችና ዕቅዶች በፆታ ፍትህ ዙሪያና በሁሉም ረገድ የወንዶችና ሴቶች መበረታታት ተግባራዊ እንዲሆን ከዚህ በላይ ያለዉን ሃላፊነት ለመወጣት ይጥራል::

## መስፈርት

ስለ ፍትህ መስፈርት ስናወራ ከዋና ዋና ጥያቄዎች ዉስጥ አንዱ ፆታዊ ጭቆናን ለወቃወም የተገለሉ እና የተጣሉ ሰዎች የሚፈልጉት ምንድነዉ? የሚል ነዉ::

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የፆታ ፍትህን በተመለከተ የባህሪ ለዉጥንና ድርጅታዊ መዋቅርን ለመለካት አመልካች ናቸዉ::

- **የአትጉዳ አቀራረብ:** አለ ህብረተሰብ ወይም ሃይማኖታዊ ዕዉቀት ማንኛዉም ሁከት፣ ነፍስ መጥፋት ወይም ችሎታ ማጣት እንዳይኖር::
- **ገላጮቻችን መተርጎም:** በማህበረ ምዕመናን ዉስጥ የወንዶችና የሴቶች እኩልነት፣ የእኩልነት ተሳትፎ::
- በመሪነትና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ **የእኩልነት ተሳትፎ፤** በብዛትና በጥራት::
- በንብረት አጠቃቀም ላይ **በእኩልነት** መጠቀም::
- ደረጃዉን የጠበቀ **ሰብአዊ መብቶች እና ዉል ስምምነት** መጠቀም::

## ግብ

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲ በህብረቱና አባል ቤተክርስቲያናት፣ በማህበራነ ምዕመናን፣ በቡዲኖችና በድርጅቶች ዉስጥ የፆታ ፍትህ እንዲኖር የሚረዳ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል::

## ዓለማ፡ የፆታ ፍትህ ፖሊሲ ለምን አስፈለገ?

ፍላጎቱ በህብረተሰብ ዉስጥ የባህሪ ለዉጥ በማመጣት የፆታ ጥቃትን ለማስቀረት ነዉ:: ሁሉም ሰዉ ይህን ተገንዝቦ፣ ወንድም ሆነ ሴት ክብር እንዳለዉ አዉቆ መብቱን ጠብቆለት አብሮ ደህንነቱ የተጠበቀ ግንኙነት ዉስጥ እንዲኖር የታሰበ ነዉ::

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲ መቋቋሙ አባል አብያተክርስቲያናትንና የህብረቱ ቢሮን እንደሚመራ ይጠበቃል::

- ፖሊሲዉ በህብረቱ ዉስጥ የፆታ ፍትህን ለማስገኘት መመሪያ እንደሚሆን መገንዘብ፤
- አብያተክርስቲያናት ይህንን የፆታ ፍትህ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም ሰዉ በመሳተፍ ራሱንና እሴቱን እንዲፈትሽ ማድረግ፤
- በቤተክርስቲያን ሕይወት ዉስጥ የወንዶችና የሴቶች እኩል ተሳትፎን ማረጋገጥ፤
- ወንዶችና ሴቶች በባህላቸዉ ዉስጥ ስላላቸዉ ድርሻ እንዲወያዩ ማበረታታት፤ ደግሞም ከባህል ባሻገርም በህብረሰብና በቤተክርስቲያን መኖር ስለሚገባቸዉ ሃላፊነትና የስራ ድረሻ በመወያየት ችሎታቸዉን በመጠቀምና በፈቃደኝነታቸዉ በቤተክርስትያን አገልግሎት በእኩልነት እንዲያገለግሉ ማበረታታት፤
- በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የቤተክርስቲያን መሪዎች እንዲወያዩና ትርጉም እንዲሰጡበት በማድረግ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወንዶችና ስለ ሴቶች ምን እንደሚል፣ ድረሻቸዉንም እንዲያዉቁ ማበረታታት:: የቤተክርስቲያን መሪዎች የፆታ እኩልነትን ለመደገፍ ከሃይማኖት መሪዎችና ከዓለማዊ መሪዎች ጋር የመሥራት እድል አላቸዉ::

## ለዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ፖሊሲ ምንድነዉ?

ፖሊሲ እሴቶችን፣ የፆታ ፍትህን ለመገንዘብ አቅጣቻ የሚያሳየዉን ራዕይ የሚገለጽበት ነዉ:: ፍላጎቶችን ለማሳካት የሚረዳ የስራ አቅጣጫን የሚያሳይ ነዉ::

በህብረቱ ዉስጥ የተለያዩ የፓሎቲካ ተሳትፎ ደረጃዎች አሉ:: በአባል አብያተክርስቲያናት ረገድ፣ ህብረቱ የተዋቀረዉ የካዉንስሉና የጉባኤዉ ወሳኔዎች የጋራ ተጠያቂነት ነዉ::

ዉስጠ ደንቡ በግልጽ እንደሚጠቅሰዉ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ከአባል አብያተክርስቲያናት የተለየ በእናርሱ ላይ ስልጣን የለዉም::

ስለሆነም ፖሊሲ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የአባል አብያተክርስቲያናት የአንድነት ምስክርነት፣ ሰብአዊ መብቶችንና ፍትህን፣ ደግሞም በግላቸዉ መረዳታቸዉን ለመግለጽ አንዱ መንገድ ነዉ::

## የካዉንስል ዉሳኔዎች

በ2013 እ.ኤ.አ. ካዉነስሉ በስብሰባዉ የወሰነዉ:

- የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲ፣ መመሪያዎችንና እቅዱን፣ ስልቱንና አተገባበሩን፤
- የስራዉን ሂደት በመከታተል የዓለም ሉትራን ፌዴዴሩሽን ለካዉንስሉ በጽሑፍ ሪፖርት እንዲያቀርብ ተወሰነ::

## የሃላፊነት ደረጃዎች

በዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን መተዳደሪያ ህግ መሰረት በሚከተሉት ደረጃዎች ፖሊሲዉን በስራ ላይ ለማዋል ተቀምጠዋል፡፡

- **ጉባኤ፣ ካዉንስልና የቢሮ ሃላፊዎች ስብሰባ**

- አጠቃላይ አቅጣጫን ለማግኘት ፖሊሲዉን ይጠቀማል፡፡
- የመንግስት አካላት ፖሊሲዉን ተግባራዊ የማድረግ ሃላፊነት አላቸዉ፡፡

- **የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ቢሮ፣ ፕሮግራሙና ፕሮጀክቱ፣እንዲሁም የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የሀገር ፕሮግራሞች**

- በተቻለ መጠን ለመስራትና ስራዉን ለመገምገም ፖሊሲዊን መጠቀም አለበት፡፡

- **አባል አብያተክርስቲያናት**

- በጉባኤና በካዉንስል ደረጃ የተወሰኑትን ዉሳኔዎች በመደገፍ በአንጻሩ በስራ መተርጎሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
- የእያንዳንዱ አባል አብያተ ክርስቲያናት ራሳቸዉን ችለዉ ራሳቸዉን ማስተዳደር በእዉነቱ የሚከበር ነዉ፡፡ ሆኖም ለጋራ ተጠያቂነት አብሮ የመስራት እድላቸዉን ደግሞ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

- **ክልላዊ**

- የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲን በመጠቀም በአዉዱ ዉስጥ መስራት እድል ማመቻቸት አለበት፡፡ በየክልሉ አዉድ መሰረት ፖሊሲዉን በመጠቀም በፆታ ፍትህ ላይ በርትቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

# የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ ፖሊሲ መመሪያዎች

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የሚሰራቸዉ ስራዎች፡

1. የፆታ ፍትህን በስነ መለኮት መሠረት ሁሉም ሰዉ ክብርና ፍትህ እንዳለዉና የፆታ እኩልነትን ያሰተዋዉቃል፡፡
2. ክብርን፣ ፍትህን፣ የተሳትፎነትን፣ የጋራ ተጠያቂነትንና ግልጸኝነትን በመደገፍ የሁሉም ሰዉ ተሰጥኦን ያከብራል፡፡
3. የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ጉባኤና ካዉንስል ዉሳኔዎችን፣ በተለይ በፆታ እኩልነት ላይ በክልል ደረጃ ሥራ ላይ እንዲዉል ያደርጋል፡፡
4. የስነ-ፆታ ትንተና በሁሉም ልማት ስራና ሰብአዊ መብቶች ያረጋግጣል፡፡
5. የሴቶች አቂም ማጎልበትን ይደግፋል፡፡
6. በፆታ ፍትህ ላይ ወንዶች በንቃት እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡
7. ሴቶች በመሪነትና በዉሳኔ ሰጪነት ሙሉ ተሳትፎ እንዳይኖራቸዉ እንቅፋት የሚሆኑትን ይለያል፡፡
8. ዋና ዋና ድርጅታዊ ፖሊሲዎች፣ ልምምዶች፣ በጀት፣ የሰዉ ሃይል አስተዳደር፣ ዉክልና፣ ስልጠናና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚሰሩት አካላት የፆታን ሚዛናዊነት የጠበቀና የወንዶችና የሴቶች በእኩል መሳተፍን ያረጋግጣል፡፡
9. የፆታ ትንተና በሁሉም ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ እቅዶች፣ እቅዶችን መተግበርና ግምገማ መኖሩን ማረጋገጥ፡፡
10. ስነመለኮትን፣ ቅዳሴንና የአምልኮ ህይወትን በፆታ ፍትህ እይታ ለአገልግሎት ያዉላል፡፡



## የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ዖታ ፍትህ እቅድ

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን እቅድ የፆታ ፍትህን የመረዳት ሂደትን ያስተዋዉቃል፡ ፡ ይህ ያለዉ መመሪያ ትምህርታዊ ይዘት ያለዉና ሦስት እቅድ፣ ማየት፣ መፍረድ/መለየትና ማድረግ ናቸዉ፡፡

- **ማየት** ማለት እያንዳንዱን እዉነትና አዉድ መረዳትና ማንበብ ማለት ነዉ፡፡
- **መፍረድ /መለየት** ማለት ስለ ሰብአዊ መብቶች ለመለየት መጽሐፍ ቅዱስንና ስነ መለኮትን መጠቀም ማለት ነዉ፡፡
- **ማድረግ** ማለት እዉነቱን ካወቁና ከለዩ ቦኋላ በአንጻሩ መሥራት ወይም መለማመድ ማለት ነዉ፡፡

## የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ህብረት ወደ አካታች በሚደረገዉ ጉዞ የት ነዉ የሚቆመዉ?

### *የሴቶች መሪነትና ተሳታፊነት*

ከአስርተ ዓመታት በላይ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን በስነመለኮት በመመራት አካታችን ማለትም ሴቶችን በሁሉም ሃላፊነት በማሳተፍ ስራዉን ሲቀጥል ቆይተዋል፡፡ ይህም ቀደም ተብሎ ስለ ሴቶች ተሳትፎ በተወሰነዉ ዉሳኔ ማየት ይቻላል፡፡

- በ1952 እ.ኤ.አ. በሀኖቨር፣ ጀርመን በተካሄደዉ በዓለም ሉትራን ፌዴሽን ሁለተኛ ጉባኤ የሴቶች ክፍል በሴቶች ኮሚሺን እንዲጠቃለል ተደረገ፡፡ ይህም በ1975 እ.አ.አ. ለተቋቋመዉ የሴቶች ዴስክ አማካሪ ኮሚቴ በመሆን እንዲያገለግል ረዳዉ፡፡ የሴቶች ዴስክ እንዲፈጠር የተወሰነዉ በ1970 እ.አ.አ. በአቬነ፣ ፈረንሳይ በተካሄደዉ በአምስተኛዉ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ጉባኤ ነበር፡፡
- በ1984 እ.አ.አ. በቡዳፐስት፣ ሀንገሪ በተካሄደዉ በዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ሰባተኛ ጉባኤ የሴቶች ተሳትፎ በኮታ እንዲሆን ተወሰነ፡፡

## የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን አባል አብያተክርስቲያናት የቅስና አገልግሎት የሚሰጡ ሴቶች በመቶኛ




## የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን አባል አብያተክርስቲያናት የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የሆኑ የቅስና አገልግሎት የሚሰጡ ሴቶች በመቶ




- ጉባኤዎች፣ ካዉንስሎች፣ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ባለስልጣናት ዉሳኔ ሰጪ አካላት የወሰኑት በቅስና የሚያገለግሉ ሴቶች ተሰጥኦአቸዉ በዓለም አቀፍ አገልግሎት ወሳኝ መሆኑን ነዉ:: የሴቶች በቅስና አገልግሎት መሳተፍ በህብረቱ ዉስጥየሴቶች አካታችነት ከፍ ለማድረግ በጣም አስፈላጊ ነዉ:: የወንዶችና የሴቶች በእኩልነት በዉሳኔ ሰጪነት መሳተፍ ሌላዉ ወደ አካታችነት የሚወስድ ትክክለኛ መንገድ ነዉ::

- በኮታ ዘዴ መጠቀም በመዋቅሩ ዉስጥ የሴቶች ሙሉ ተሳትፎ ከፍ እንዲል ትልቅ ሚና አለዉ:: በተለይ በዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር ዉስጥ በዚህ ኮታ ዘዴ ማለትም በጉባኤዎችና በስበሰባዎች ተሳትፎ ዉስጥ መጠቀም የሴቶች ሙሉ ተሳትፎን እያሳደገ እንደሚሄድ ተረጋግጠዋል::

- በዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን በኩልም ሴቶችና ልጃገረዶች በህብረቱ ዉስጥ የዲቁና አገልግሎት በማገልገል ጥሩ ነገር እንዲኖር አስተዋጽኦ ያደርጋል::

- በዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ጎልቶ ከሚታዩት ህይወት ዉስጥ አንዱ የቤተክርስቲን ትንቢታዊ ድምጽ፣ ለሴቶች ጭቆናና ጥቃት፣ ለብጥብጥ፣ ለሁከት እምቢ በል! የሚል ነዉ::

  ይህም የሚያመለክተዉ በቤተክርስቲያን ዉስጥም በተወሰኔ መልኩ ጥቃትና ጭቆና መኖሩንና ይህንንም እንዴት መቅረፍ እንደሚቻል መመካከር እንደሚያስፈልግ ነዉ::

- በሴቶች ላይ የሚደርሰዉን ጥቃት ለመዋጋት የሚሰሩት አብያተ ክርስቲናትና ቤተክርስቲያን ነክ

ድርጅቶች ፍትህን ለማስፈን በሚሰራዉ ስራ ላይ ይመሰረታል፡፡

## የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ወደ ፆታ ፍትህ ጉዞ

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህን ለማስፈን ጉዞዉን ቀጥለዋል፣ ስራዉን ለማከናወንም መንገድ እያበጀ ይሄዳል፡፡ ይህም ፍትህ በድርጅትና በመዋቅር ደረጃዎች ሁሉ ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡

- በ1997 እ.አ.አ. በሆንግ ኮንግ በተካሄደዉ በዘጠነኛ ጉባኤ፣ የፆታ እኩልነት እንደ አንድ ዋና የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ስራ መሆኑ እፋ ሆኖ ታወቀ፡፡
- በ2003 እ.አ.አ. በዊኒፔግ ካናዳ የተካሄደዉ በአስረኛ ጉባኤ፣ ከዚህ በፊት የተወሰኑትን ጉዳዮች በመከለስ፣ እንደገናም በመወያየት ተጨማሪ ዉሳኔ አስተላልፈዋል፡፡ ዉሳኔዉም የሴቶችና የወጣቶች በቤተክርስቲያንና በህብረቱ ዉስጥ ሙሉ ተሳትፎ ነዉ፡፡
- የቤተክርስቲያን የዲቁና አገልግሎት ስነመለኮትን መሰረት ባደረገና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጸፈዉ ወደ መሬት ወርዶ ተግባራዊ ሆኖ ባለንጀራን በሚያስፈልገዉ ማገልገሉ ላይ ነዉ፡፡ በዚሁ ዲቁና አገልግሎት ቤተክርስቲያን ለተጨቁኑትና እርዳታ ለሚያስፈልጋቸዉ፣ ለተገለሉ፣ ለተጣሉ ድምጽና ጠበቃ በመሆን ተልዕኮዋን ትፈጽማለች፡፡



- ይህም ከተሰጠላት ተልእኮዎች አንዱ ነዉ፡፡ ማለት ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ከተባለዉ ዉስጥ ሲሆን ቤተክርስቲያን ራሷ ካለችበት ተነስታ ወደ ሌሎች እርዳታ ለሚያስፈልጋቸዉ በመሄድ፣ ድምጽ ላጡ ድምጽ በመሆን፣ ለተጨቆኑት ጠበቃ በመሆን እንዲትሞግትላቸዉ የተሰጣትን ተልዕኮ መወጣት አለባት፡፡

- በዚህ ዲቁና ተልእኮ ነው የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የሰብአዊ መብቶችንና የሁሉም ሰዉ እኩልነት ላይ በመስራት በሁሉም እንዲታወቅና እንዲሰራበት ያደርጋል፡፡ በዚህም ሴቶች በመሪነት የሙሉ ተሳታፊነት እንዲኖተራቸዉ ያደርጋል፡፡

- በ2009 እ.አ.አ. ስለ ስነ-ፆታና ስልጣን በመጽሐፍ ታተመ፡፡ የመጽሐፉም ርዕስ "It will not be so among you!" በእናንተ መካከል እንዲህ አይሆንም፣ የሚል ነበር፡፡ ይህም በአራተኛ ጊዜ በስነ-ፆታ ላይ የተደረገና በካዉንስል ተቀባይነትን ያገኘ ነበር፡፡

- ከዚህም በላይ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን እንደ አብያተክርስቲያናት አከል የፆታ ፍትህ ፖሊሲን በማርቀቅ ላይ በርቶት ሲሰራ ነበር፡፡ በዚህም አባል አብያተክርስቲያናት በሰብአዊ መብቶች ላይ እንዲሰሩ ፍንጭ በማግኘት ይሰሩበታል፡፡

## መጽሐፍ ቅዱሳዊና ስነ መለኮታዊ መሠረት፡ የፆታ ፍትህ ለሉትራዊያን ለምን አስፈላጊ ሆነ?

የፆታ ፍትህ ፖሊሲን ማርቀቅና ማዘጋጀት ለዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን እግዚአብሔር ወደ ዓለም ሂዱ ብሎ ሁለንተናዊ ተልዕኮ የሰጠዉን የመረዳትና ተግባራዊ የማድግ ሂደት አካል ነዉ፡፡ የእኩልነትና ፍትህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታ በዚህ ፖሊሲ መጀመሪያ አካባቢ በገጽ 5 እንደ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የፆታ ፍትህ መረዳት ተጽፎአል፡፡ ሁሉም ሰዉ፣ ወንድና ሴት፣ በእግዚአብሔር አምሳል ነዉ የተፈጠረዉ፡፡ የተለያዩ ናቸዉ፣ ደግሞም እኩል ናቸዉ፡፡ ሴቶችም ወንዶችም እግዚአብሔር የፈጠራቸዉን ፍጥረታት የመጠበቅና የመንከባከብ እድልና ሃላፊነት አላቸዉ፡፡ የሰዉ ዘር በእግዚብሔር ይደገፋል፣እናም እርስ በርስ ማገልገል አለበት፡፡ የስነ-ፆታ መሳሪያዎችን በመጠቀም የፍጥረት

ታሪኮችን ለመተርጎም አስፈላጊ የሆኑትን ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ያደርጋል፡፡ ጥያቄዎቹም፡-

- እግዚአብሔር አስቀድሞ ከሰዉ ዘር በሙሉ ጋር ግንኙነት ለማድረግ የፈለገዉን ወንዶችና ሴቶች እንዴት ይቀበላሉ?
- ሴቶችና ወንዶች በሚቀጥሉት የፍጥረት ስራ እንዴት የእግዚአብሔር የስራ ባልደረባ ይሆናሉ?
- በፍጥረት እኩልነትና በባለአደራነት እኩልነት ላይ ያለዉ ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ሀሳብ ስለ ሽርክና ወይም አብሮ መስራት እንዴት ይተረጎማል?
- በእናንተ ባህል የእግዚአብሔር ፀጋ ባለአደራነት ምን ማለት ነዉ?
- በእናንተ ባህል አዉድ ባለአደራነት በሴቶችና በወንዶች ፍትህ ላይ ያለዉ እንድምታ ምንድነዉ?

የሚከተሉት የተወሰኑ የሉትራዊያን ስነመለኮት መነሻ ነጥቦች ናቸዉ፡፡ እነዚህም የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን አባል አብያተክርስቲያናት በፆታ ፍትህ ላይ እርስ በርሳቸዉ ሀሳበ የሚለዋወጡና አቋማቸዉን የሚያጠነክሩበት ነዉ፡፡

## ቅዱሳት መጻሕፍት፡ በጥቅስና በሕይወት መካካል ያለዉ ቃለ ምልልስ

መጽሐፍ ቅዱስ ለምን አስፈለገ? መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ፀጋ ዓለም ዉስጥ ላሉት ይናገራል፡፡ ሉተር ክርስቲያኖችን ሲያስታዉስ፣ በጣም አስፈላጊዉ ነገር የእግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ቃል የገባዉ ፀጋ ነዉ፡፡ ስለዚህ በሉትራን ባህል ቁልፍ የሆነዉ ጥያቄ፣ ክርስቶስን የተሸከመዉ ማን ነዉ? በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር ፀጋ እንዴት ይገለጣል? ይህ በወንጌል በምሳሌ ተገልጾአል፡፡ ኢየሱስ ኀባጣ የነበረችዉን ሴት ሲፈዉሳት ሁለመናዋ ተፈወሰ (ሉቃ 13፡10-17).

እነዚህ ሀሳቦች ወደ ሌሎች ጥያቄዎች ይመራሉ፡፡ ጥያቄዎቹም፣ የእግዚአብሔር የፆጋ ቃል ኪዳን ለወንዶችና ለሴቶች ምን ማለት ነዉ? የእግዚአብሔር ፀጋ እንዴት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስን በስነ-ፆታ እይታ ለመተርጎም ያግዛል?

የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክቶችን የመተርጎምና ወደ አዉዳችን አምጥተን ተግባር ላይ የምናዉልበት ጥበብ ሄርሜኑቲክስ ይባላል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ አተሮጓጎም ሉትራን አስፈላጊ ሆኖ የታያቸዉን የተለያዩ አስተምሮዎች አላት፡፡ እነዚህም ሁሉም ክርስቲያኖች ካህናት መሆናቸዉን፣ ጽድቅ በእምነትና በፀጋ፣ የወንጌልና ሕግ ልዩነት፣ መዳን በክርስቶስ ብቻ፣ የመስቀል ስነመለኮትና የመጽሐፍ ቅዱስ በራሱ ራሱን መተርጎም ወይም መፍታት ናቸዉ፡፡



በሉትራዊያን ዉስጥ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም መንገዶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል አዉዳዊ ንባብና ትርጓሜ ሲሆን ከጥቅሱ ጋር ቃለ ምልልስ ለማድረግ አዉዱንና ህብረተሰቡን መነሻ የሚያደርጉበት መንገድ ነዉ፡፡

ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ጋር በማያያዝ የራሳቸዉን የቀን ተቀን ትግላቸዉን ማየት ይጀምራሉ፡፡ ከጥቅስ ጋር ያለዉ ግብግብ በፆታ ኢፍትሃዊ ላይ ጥያቄ እንድናነሳ ያነሳሳናል፡፡ የፆታ ፍትህ ጉዳይ ስነመለኮታዊ መሰረት አለዉ፡፡ ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምስክርነቶች ነዉ፡፡

የተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ስለ ተገለሉ ሴቶች እነደገና ሁሉም ሰዎች በእግዚአብሔር ዓይን እኩል እንደሆኑ ከሚናገረዉ ክፍል ጋር በማያየዝ በማንበብና በመተርጎም በፆታ ፍትህ ላይ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለማድረግ

ደግሞ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ መስራት ያስፈልጋል፡፡

- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍትህ ምን ይላል?
- የትኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ናቸዉ ስለ ፆታ ፍትህ የሚደግፉት?
- የትኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ናቸዉ ስለ ፆታ ፍትህና የፆታ እኩልነትን የሚቃወሙት?
- እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማንበብ የእግዚአብሔር ፀጋ ምን ዓይነት ትርጉም ይኖረዋል?

## ጽድቅና ፀጋ፡ ነፃነትና ክብር ለሁሉም የሰው ዘር

- ➢ መጽደቅ ምን ዓይነት ስሜት አለዉ?
- ➢ እንደ ግለሰብ በአንድ ጊዜ ጻድቅ መሆንና ኃጢአተኛ መሆን ምን ስሜት አለዉ?
- ➢ ለግለሰብና ለቤተክርስቲያን በአንድ ጊዜ ጻድቅ መሆንና ኃጢአተኛ መሆን የሚያስከትለዉ ዉጤት ምን ምን ናቸዉ?

በፀጋ መጽደቅ የሉትራን ማንነት መግለጫ ነዉ፡፡ መጽደቅ ማለት ከታሰርነበት ነጻ መሆን ማለት ነዉ (ሮሜ 5)፡፡ በተጨማሪም በዚህ ምድር ላይ እያለን ከኃጢአት ነጻ ሆኖ መኖር ስለማይቻልና በአቅማችን ከኃጢአት ነጻ ሆነን መኖር በፍጹም ስለማይቻለን እኛ በአንድ ጊዜ ጻድቃንና ኃጢአተኞች ነን፡፡ ይህ በሉትራን እይታ ቤተክርስቲያን ዉስጥ በጽድቅ እንኖራለን በህበረተሰብ ዉስጥ ስንኖር ደግሞ ኃጢአተኞች እንሆናለን፡፡

ሰዉ መሆናችን በፍጥረታችን ብቻ እኩል የሆነን ሳይሆን በኃጢአትም እኩል ነን፡፡ ጳዉሎስ በመልዕክቱ፣ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፡፡ ሁሉ ኃጢአትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጉድሎአቸዋል፡፡ (ሮሜ 3፡10-11፣ 23)

ኃጢአት በግለሰብ ብቻ የሚሰራ መስሎ ቢታይም፣ ህብረተሳብና ድርጅቶችም ራሳቸዉን መመርመር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ኃጢአት በሌሎች ላይ ክፉ ማደረግ ነዉ፣ በራሳችንና በእግዚአብሔርም ላይ ክፉ መሆንን ያጠቃልላል፡፡

ሕጎች፣ ልምምዶች፣ ሀሳቦች፣ አመለካከቶችና ፖሊሲዎችም ሌላዉን የሚጉዱ ከሆኑ፣ የእግዚአብሔርን ፍጥረት የሚጉዱ ከሆኑ ኃጢአት ናቸዉ፡፡ ስለዚህ ኃጢአት በግለሰብ ብቻ የሚሰራ ሳይሆን በመዋቅርና በድርጅትም ይሰራል ማለት ነዉ፡፡

ማንኛዉም ሰዉ ወይም ድርጅት የሌላዉን ዋጋ ከሌሎች አስበልጦ የሚያሰቀምጥ ከሆነ ኃጢአተኛ ነዉ፣ ምክንያቱም ሌሎችን ዝቅ ማድረግ ጎጂ ነዉና፡፡ በዚህም አንጻር ወንዶች በሴቶች ላይ የበላይነትን ማንጸባረቅና በእነርሱ

ላይ አሉታዊ ጫና ማድረግ ኃጢአት ነዉ።

በእምነት በፀጋ በኩል መጽደቅ የክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ መኖር ሁኔታን ይቀይራል። በመሆኑም ቤተክርስቲያን በዚህ ምድር ኢፍትሃዊነት አሰራር መኖሩን ትገነዘባለች። በወይን አትክልት ሠራተኞች ታሪክ (ማቴ 20፡1-16) የእግዚአብሔር ፀጋ ለሁሉም ሠራተኞች እኩል ተሰጣቸዉ፣ ምክንያቱም ክብራቸዉ ታድሶአል. ስለሆነም ሁሉም ሰዉ በእኩል ተዋጅተዋል።

- እነዚህ ሠራተኞች በአኩል በመስተናገዳቸዉ ምክንያት በእነርሱ ሕይወት ዉስጥ ምን ምን ለዉጦች ይሆናሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?
- ሁሉም በእግዚአብሔር ፀጋ ስለ ጻደቁ በማህበረሰብ ዉስጥ ምን ምን ለዉጦች ይሆናል?



## የእግዚአብሔር እንደ ሰዉ ሥጋ መልበስ፡ አርአያና ፍትህ

- በእግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ አርአያ መሆንና በፍትህ መካካል ምን ምን ትስስሮችን ታያላችሁ?
- የሰዉ አርአያነትና በፍትህ መካካል ምን ምን ትስስሮችን ታያላችሁ?

እግዚአብሔር ሥጋዉን በመልበስ የሰዉን ሕይወት ሙሉ በሙሉ ተካፈለ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ከሰዉ ጋር ይገናኛል።ኢየሱስ ክርስቶስም እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ለሰዉ ያሳያል። እርሱ የሚያሳየዉ እግዚአብሔር ደግሞ ሕዝቡን ከባርነትና ከዚህ ከፉና የወደቀ ዓለም ሀሳብና ቀንበር ነጻ ማዉጣት የሚፈልግ አምላክ ነዉ። የተጨቆኑትንና ዲሆችን የሚረዳ፣ ሁሉም ሰዉ እንደ እግዚአብሔር ልጆች በነጻ እንዲኖር ጥሪ ያቀርባል።

እግዚአብሔርም የለቅሶአቸዉን ድምጽ ሰማ፣ እግዚአብሔርም ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር ያደረገዉን ቃል ኪዳን አሰበ። እግዚአብሔርም አለ፣ በግብጽ ያለዉን የሕዝቤን መከራ በእዉነት አየሁ፣ ከአስገባሪዎቻቸዉም የተነሳ ጩኸታቸዉን ሰማሁ፣ ስቃያቸዉንም አዉቄአለሁ።(ዘጸ 2፡24፣ 3፡7). ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት ጠራቸዉ። የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆን በትዉልድ ሀረግ ሳይሆን በመንፈሳዊነትና ፈቃዱን በመፈጸም ነዉ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰለዚህ ነገር ሲናገር ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፣ እርሱ ወንድሜ ነዉ እህቴም እናቴም አለ። (ማር 3፡35) እግዚአብሔር የሰዉን ሥጋ ለብሶ ልክ እንደ ሰዉ በመሆን ሰዉ በሥጋዉ የሚያሳልፈዉን ሁሉ፣ ከኃጢአት በስተቀር፣ ተካፈለ። ይህም የሆነዉ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ነዉ እዉነት የሆነዉ። ቃልም ሥጋ ሆነ፣ ጸጋንና እዉነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ (ዮሐ 1፡14)።

የክርስቶስ አካል በመንፈስ ቅዱስ ሃይል አማካይነት ቤተክርስቲያን ነዉ። ዛሬም እዉነተኛ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት።

አንድም ብልት ቢሰቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሰቃያሉ፣ አንድ ብልትም ቢከበር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል፡፡ እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ፡፡ (1ቆሮ 12፡26-27)

በዚህ ምድር ላይ በአካል ያለች ቤተክርስቲያን ፍትህን ለዚህ ዓለም በግልጽ እንዳታሳይ መንፈስ ቅዱስ ያግዛታል፡፡

- የእግዚአብሔር የሰዉን ሥጋ መልበስና በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚያስፈልገዉ ፍትህ እንዴት ይገናኛል?

## ቅዱሳት ሚስጥራት፡ሁለቱንም ፆታ ያካተተ አግለግሎት በጠረጴዛ ዙሪያ ማገልገል

- እግዚአብሔር በቅዱሳት ሚስጥራት ቃል የገባዉ ነጻነት ምን ዓይነት ነዉ?
- ቅዱስ ቁርባን ሲከበር በክርስቶስ አካል ዉስጥ ምን ዓይነት ልዩነቶችን ትገነዘባለህ?

በጥምቀት እያንዳንዱ ሰዉ የክርስቶስ አካል ይሆናል (1ቆሮ 12)፡፡እያንዳንዱ ሰዉ አስፈላጊ ነዉ፣ ሁሉም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አለዉ፡፡

ኢየሱስ ከተጨቆኑት ጋር፣ ከተናቁት ጋር ተቀምጦ ከእነሱ ጋር ደቦ ቆርሶ በላ፡፡ በክርስቶስ ልዩነት የለም፣ ሁሉም አንድ ናቸዉ፡፡ በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፣ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና፡፡ (ገላ 3፡26-27) አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን፣ እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና፡፡ ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል፡፡ (1ቆሮ 12፡13)

ጳዉሎስ አሁንም የገላትያ ሰዎችን ስያስታዉስ፤ በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻ አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ፡፡ (ገላ 5፡1)

የሁሉም አማኞች ካህናት መሆን ማለት ነጻ የወጡ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ነጻ ያልወጡትን ነጻ እንዲያወጡና ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲገቡ እንዲያደርጉ በመንፈስ ቅዱስ የተጠሩ ማለት ነዉ፡፡

- ጥምቀትና ቅዱስ ቁርባን እንዴት አዲስ ሕይወትን ለመኖር ያደርጋል?
- በአዉድህ ዉስጥ ምን ዓይነት መሪነት ነዉ በመካፈል የሚሰራዉ?



## የቤተክርስቲያን ምሦሦዎች፡ መሪነት መጋራትና የእኩልነት ደቀ መዝሙርነት

- ጥምቀት በደቀመዝሙርነትና በመሪነት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርገዉ በምን መንገድ ነዉ ብለህ ታስባላችሁ?

- እንደ ቤተክርስቲያን ስለ ሴቶች መሪነት ለሚቃረኑ ጥቅሶች እንዴት መልስ እንሰጣለን?

በጥምቀት አማካኝነት ወንዶችም ሴቶችም ታድሶ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቆአል፡፡እግዚአብሔር ሁለቱንም ሙሉ በሙሉ ተቀብሎአቸዋል፡፡ ሁለቱም ፆታዎች በኃጢአትም በጽድቅም አንድነት አላቸዉ፡፡

የሴትን ተፈጥሮ ታሪክ አንስቶ ሰዎች እሷ እኮ ወንድን ለመርዳት ነዉ የተፈጠረችዉ ብሎ የወንድ የበላይነትን ይከራከራሉ፡፡ ክፍሉን ስናነብ እንዲህ ይላል፣ እግዚአብሔር አምላክም አለ፣ ሰዉ ብቻዉን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፣ የሚመቸዉን ረዳት እንፍጠርለት፡፡ (ዘፍ 2፡18) በዚህ ክፍል ረዳት የሚለዉን እናያለን፡፡

ይህን ቃል ከሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልም እናነባለን፣ ዓይኖቼን ወደ ተራሮች አነሳሁ፣ ረዳቴ ከወዴት ይምጣ? ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነዉ፡፡ (መዝ 121፡1-2) በዘፍጥረት ዉስጥ ለሴት የወንድ ረዳት እንዲትሆን የተጻፈና በዚህ ስፍራ የተጻፈዉ ቃል ተመሳሳይ ነዉ፡፡

በዚህ ጥቅስ መሰረት ረዳት የሚለዉ የአንዱ በላይነት ሳይሆን እርስበርስ መደጋገፍን ያሳያል፡፡

ሌላዉ ሴቶች ዝም እንዲሉ የተነገረዉ መመሪያ፣ ሴቶች በማህበር መካከል ዝም ይበሉ፣

ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸዉምና፡፡

(1ቆሮ 14፡34) ይህ በሌሎች ቦታዎች ከተከለከለዉ ተለይቶ መነበብ የለበትም፡፡ በሌላ ስፍራ፣ የሚተረጉም ባይኖር ግን በማህበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር፡፡ ይላል (1ቆሮ 14፡28) በተጨማሪም፣ በዚያ ለሚቀመጥ ለሌላ ግን አንድ ነገር ቢገለጥለት ፊተኛዉ ዝም ይበል፡፡ ይላል (1ቆሮ 14፡30)

የሴቶች ዝም የማለት መመሪያ በቆሮንቶስ አምልኮ ፕሮግራም ችግር የተነሳ መሆኑን በመገንዘብ አስፍተን ማየት ያስፈልጋል እንጂ እንደ ዘለዓለም መመሪያ አድረገን መዉሰድ የለብንም፡፡ ምክንያቱም ጳዉሎስ ራሱ ሲጽፍ፣ ራስዋን ሳትሸፍን ግን የምትጸልይ ወይም ትንቢት የሚትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን ታዋርዳለች፣ እንደ ተላጨች ያህል አንድ ነዉና፡፡ (1ቆሮ 11፡5) ሴት አገልጋዮች በብሉይ ኪዳንም በአዲስ ኪዳንም ነበሩ፡፡

- ማሪያም ነብይትዋ፣(ዘፀ 15፡20) ከሙሴና ከአሮን ጋር ስትሰራ የነበረች፡፡
- ዲቦራ፣ የፐሎቲካም የሃይማንትም መሪ የነበረች (መሳ 4፡4)፡፡
- ሃና፣ ነብይትና ስለ ኢየሱስ መሲህነት የኢየሩሳልምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ እርሱ ትናገር ነበር (ሉቃ 2፡36-38)፡፡
- የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ የመጀመሪያ መስካሪዎች፣ መቅዳላዊት ማርያም፣ ዮአና፣ ሱዛና (ሉቃ 8፡2-3፣ ማር 15፡41)
- ጳዉሎስን በአገልግሎት ሲደግፉና ሲረዱ የነበሩ ሴቶች፣ ጵርስቂላ (ሮሜ 16፡3)፣ ጁኒያ (ሮሜ 16፡7).

## እቅዱን በአውድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መመሪያዎች ቁጥጥርና ተጠያቂነት፡

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ቢሮ እንደ ድርጅት የተቋቋመዉን ለመከታተል ሃላፊነት አለዉ፡፡ የሥራ ሂደቱ ለካዉንስል በጠቅላይ ጸሐፊዉ ይሰጣል፡፡

ይህ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ፍትህ ፖሊሲ የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ህብረት ያለበት ቦታ ሁሉ እንደ መመሪያ ያገለግላል፡፡ የሴቶች በመሪነት መሳተፍና የሁሉም ሰዎች ክብርና ሰብአዊ መብት ሁሉ በዚህ መመሪያ ክትትል ይደረጋል፡፡



## የስነ-ፆታ ትንተና፡

- በወንድና በሴት መካከል ያለዉን ልዩነት እዉነቱን መገንዘብ፣
- የልዩነቶቹ ፈተና ወደ ህብረተሰብ፣ እኮኖሚ፣ ፕሎቲካና ሃይማኖት ኢፍትሃዊነት ይመራል፣
- በፆታ ላይ የተመሰረተ የሥራ ክፍፍልና የወንድና የሴት ምንነት ለመለየት የሚረዳ መሳሪያ ነዉ፡፡

ከስነ-ፆታ ትንተና የሚጠበቀዉ ግብ ያለዉን ማበላለጥ ቀይሮ ወደ እኩልነት፣ በወንዶች /ወጣት ወንዶችና ሴቶች /ልጃገረዶች ወደ ትክክለኛ ግንኙነት ማምጣት ነዉ፡፡ ስለዚህ ማድረግ የሚያስፈልገዉ፡

1. የግልና የድርጅት የስነ-ፆታ መረጃ መሰብሰብና መተንተን፣
2. በትንተናው መሰረት ለፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች መሰረት መጣል፣
3. የስነ-ፆታ ትንተናን በመጠቀም ፆታን መሰረት ያደረገ የንብረት አጠቃቀም፣ ስለጣን መጋራትና ዉሳኔ ሰጪነት ያለዉን ችግር መረዳት፡፡

## አሳታፊነት

ፆታን መሰረት ያደረገ ጭቆና ቶሎ መፍትሔ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ አዲስ ግንኙነትን መመስረትና በፊት የነበረዉንም ማጠንከር ለዉጥ ለማምጣት ዋና መፍትሔ ነዉ፡፡

በተግባር ደረጃ ተሳታፊነት በፕሮግራሞችና በፕሮጀክቶች፣ እንዲሁም በአባል አብያተ ክርስቲናት ይረጋገጣል፡፡ ይህም ተግባራዊ የሚሆነዉ:

1. ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ ቁጭ ብሎ, አንድ ላይም ተለያይቶም ለየብቻም ስለ ማንነታቸዉና ልምምዳቸዉ እወነቱን እንዲያዉቁ፣ ገለጻ ሲሰጣቸዉም በጥልቀት እንዲያዳምጡ፣ ሀሳብ እንዲሰጡበት፣ ሲነጋገሩ ደግሞ እርስ በርስ እንዲግባቡ ቦታና ሁኔታ ማመቻቸት፡፡
2. ወንዶችና ሴቶች አብሮ እንዲሰሩ ሥራ ማዘጋጀትና ሥራዉን ማስተዋወቅ፣ ለምሳሌ የግጭት አፈታት ዘዴ፣
3. የወንዶችና የሴቶች፣ የወጣት ወንዶችና ወጣት ሴቶች/ ልጃገረዶች ፍላጎታቸዉ በፕሮግራሞችና በፕሮጀክቶች በትክክል መድረሳቸዉን፣ እንዲሁም ሁሌቱም ወንዶችና ሴቶች በሥራቸዉ ዉጤታማ ሆኖ መገኘታቸዉን ማረጋገጥ፡፡

## አቋራጭ የፆታ ፍትህ

የፆታ ፍትህ አቋራጭነት መግለጽ የመጀመሪያ ፐሎቲካዊና ስልታዊ ምርጫ ነዉ፡፡ ማንኛዉም አካሄድ፣ መዋቅር፣ እቅድ፣ ፕሮግራም እና ፕሮጀክት ለጾታ ፍትህ ነዉ ተጠያቂነቱ፡፡

የሚከተሉት በህብረት ዉስጥ የአቋራጭ የፆታ ፍትህ የተወሰኑ ደረጃዎች ናቸዉ፡፡

1. የፆታ ፍትህን እንደ መሣሪያ በመጠቀም ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ማቀድና ህጎችን፣ መመሪያዎችን፣ ዶኩመንቶችን፣ የሰዉ ሃይል ፖሊሲዎችን፣ የቋንቋ ፖሊሲዎችን ማቀድ፡፡
2. የፆታ ተኪታ አመልካቾችን በመጠቀም የወንዶችና የሴቶች ጥቅምና ጉዳት መለካት፡፡
3. በድርጅት ዉስጥ ሂደቱን ለመቆጣጠር ትኩረት የሚደረግባቸዉን ሰዎች ማዘጋጀት፡፡
4. ስለ ፆታ ፍትህ ስነ-መለኮታዊ ገለጻ ማስተዋወቅ፡፡

## ችሎታን ማሳደግ

ሴቶችና ወንዶች በመሪነትና በዉሳኔ ሰጪነት መሳተፍ እኩል መብት እንዳላቸዉ ግልጽ ነዉ:: ሴቶችና ወንዶች ዋጋ እንዳላቸዉ ማወቅ የሚያሳየዉ ቤተክርስቲያን ወንዶችና ሴቶች ግዳጅና ሃላፊነቶችን እንዲጋሩ ለማድረግ እንደሚትሰራ ነዉ:: ይህን በማድረግ ቤተክርስቲያን አርአያ ትሆናለች::

## በፆታ ፍትህ አመለካከት የአቂም ግንባታ እቅድ፡

1. ስለ ሴቶች ጥቃት በሁሉም እንዲታወቅ ማድረግ::
2. በፆታ እኩልነት ላይ ትኩረት በማድረግ የወንዶችና የሴቶች እኩልነት እንዲታወቅ ማድረግ::
3. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡዲንን መደገፍ፤ በተለይ ስለ ስነ-ፆታ ከመጽሐፍ ቅዱስ መወያትን ማበረታታት::
4. የፆታ ፍትህን በሴሚናሪዩም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለማስተማር በትምህርት ካርኩለም ዉስጥ እንዲገባ ማድረግ::
5. በቤተክርስቲያንና በህብረተሰብ ዉስጥ የፆታ ፍትህ እንዲኖር ለአስተማሪዎች፣ ለመጋቢያን፣ ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ፣ ለበጎ ፈቃደኞችና የቤተክርስቲያን ሠራተኞች በመደበኛነትና መደበኛ ባልሆነ ደረጃ ስልጠና መስጠት::
6. በስነ-መለኮት ትምህርትና ጥናት ዉስጥ ሴቶች በሙሉ ተነሳሽነት እንዲሳተፉ ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት::
7. በመገናኛ ብዙሃን በመጠቀም ሰዎች ስለ ስነ - ፆታ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ማድረግ::
8. ወጣት ሴት መሪዎችን ለማፍራት የአቂም ግንባታን መገንባት::
9. በአስታፍ ዉስጥ ተከታታይ መማር እንዲኖር ዝርዝር ዘዴን ማዘጋጀት::
10. በሁሉም ደረጃ በድርጅት መዋቅር ዉስጥ ወንዶችና ሴቶች በእኩልነት መሳተፋቸዉን ማረጋገጥ::

## ድርጅታዊ አደረጃጀቶች

የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን በስራዉ ልዩነትና አንድነትን ያጠቃልላል:: ይህ ማለት እቅዶችን በማዉጣትና ተግባራዊ በማድረግ በተለያዩ ቡዱኖች የተለያዩ ወንዶችና ሴቶች ዉስጥ አብሮነትና አንድነት እንዲኖር ያደርጋል:: በቤተክርስቲያንም ዉስጥ የወንዶችም የሴቶችም ተሳትፎ፣ በተለይም በእኩልነት በመሪነትም እንዲሳተፉ ያደርጋል::

በቤተክርስቲያን ዉስጥ ልዩነትም አንድነትም እንዳለ መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ:: አንድነቱ የክርስቶስ አካልነት ነዉ:: በቤተክርስቲያን ዉስጥ ያሉ ወንዶችም ሴቶችም የክርስቶስ አካል ናቸዉ::

ስለዚህ እንደ ክርስቶስ አካል ሁሉም አንድ ናቸዉ:: በእኩልነትም በአገልግሎቱ፣ በመሪነቱና በማንኛዉም ሥራ ወንዶችም ሴቶችም መሳተፍ አለባቸዉ::

ይህ በትክክል የማይከናወንበት ቤተክርስቲያን ተሃድሶ እንደሚያስፈልገዉ ግልጽ ነዉ:: በቤተክርስቲያን ዉስጥ የሴቶች በስነ-መለኮት ተሳትፎ መረጋገጫዉ ብዙን ጊዜ የሴቶች ቅስና ነዉ::

ሴቶችን በቅስና አገልግሎት ማሳተፍ የሚጠቅመዉ የፆታ ፍትህ በቤተክርስቲያን ተግባራዊ ለማድረግ በመሆን ነዉ:: ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ፡

1. በህብረትና በቤተክርስቲያን አባላት መካካል የባህሪ ለዉጥ እንዲኖር ዉይይትን ማበረታታት፣
2. ለሁለቱም ፆታዎች እኩል እንዲከፈል የተሰራዉ በ2012 በዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ቢሮ ዉስጥ የተገኘዉን ደረጃዉን የጠበቀ የደመወዝ አከፋፈል የምስክር ወረቀት ማሳደስ፣
3. በፆታ ሚዛናዊነት ላይ በ11ኛ ጉባኤ በተወሰነዉ ዉሳኔ መሰረት የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ሰራተኞች በማንኛዉም ስብሰባ፣ ኮሚቴና ስራ ዉስጥ ሁለቱም ፆታዎች በእኩልነት እንዲሳተፉ የተወሰነዉን ተግባራዊ ማድረግ፣
4. የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን ሰራተኞች ያለምንም ታቅቦ የሚደርሰዉን የስነ-ምግባር ችግር እንዲያጋልጡና እንዲቃወሙ ማድረግ፣
5. የስነ-ፆታ ኦዲትን ለድርጅቶችና ለአጋር ድርጅቶች ተግባራዊ ማድረግ፣
6. በድርጅቱ ዉስጥ የተበጀተዉ ባጀትና የተዘጋጀዉ ፕሮግራም ፆታን ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥ፣

7. በድርጅት ዉስጥ ስለ ስነ-ፆታ በቅርበት የሚከታተል ቡዱን እንዲኖር በሃላፊነት ስራዉን የሚያከናዉን ከድርጅቱ አባላት ቡዱን ማቋቋም፣

8. በመሪነትና ዉሳኔ ሰጪነት ሁለቱም ፆታዎች በእኩልነት መሳተፋቸዉን ማረጋገጥ ናቸዉ፡፡

## ደህንነትና ማስፈንና ህብረትን መፈወስ

ፆታን መሰረት ያደረገ እያንዳንዱ ጥቃት በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረዉን ይጉዳል፣ ደግሞም አብሮ በአንድነት እንዲኖሩ የተጠሩት አማኞችን ያዉካል፡፡ ስለዚህ ዝምታ መሰበር አለበት፡፡

የቤተክርስቲያን ትንቢታዊ ድርሻ ህብረትን ለማዳንና ደህንነትን ለማስፈን ሂደቶችን ማዘጋጅት ያስፈልጋል፡፡ በዚህም የተጉዱትን መፈወስ ይቻላል፡፡

ሁለንተናዊ አገልግሎት ማገልገል ያስፈልጋል፡፡ ሁለንተናዊ ተልዕኮና አገልግሎት ማለት ደግሞ ፆታ ነክ ጥቃቶችን ለመቅረፍ መትጋት ማለት ነዉ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ወንዶች በዚህ አገልግሎት ተሳታፊ በመሆን ጥቃቱን ለማስቀረት ዉይይት ያደርጋሉ ማለት ነዉ፡፡

ምንም እንኳ የተለመደ፣ በስፋት የሚካሔድ ልማድና ባህል ቢሆንም፣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጭቆናና ጥቃት ወንጀልና ሐጥአት ነዉ፡፡ ፆታን መሰረት ያደረገ ጭቆናና ጥቃት የወንጌል ተቃራኒ ናቸዉ፡፡

እንደ እምነት አካል ጉዳይ ፆታን መሰረት ያደረገ ጭቆናና ጥቃትን ለማስቀረት የሚያስፈልጉ እቅዶች፡-

1. የፆታ ፍትህን ለማተግበር አዲስ ህጎችን፣ ፖሊሲዎችንና ልምምዶችን ማዘጋጀት፣

2. ለጭቆናና ጥቃት እንዳይዳረጉ ለማድረግ ለወንዶችና ለሴቶች ምቹ ስፍራ እንዲኖራቸዉ በሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ዉስጥ መግባት፣ መሳተፍ፣

3. የፆታ ፍትህን ለማስተዋወቅ በድርጅቶች፣ በመንግስትና መንግስታዊ ባለሆኑ ድርጅቶች፣ በተባበሩት መንግስታት መካካል ግንኙነቶችንና መሪነት ማስተዋወቅና ትስስር መፍጠር፤

4. በዓለም ሉትራን ፌዴሬሽን የሥራ ዕቅድ ወስጥ እንዲካተቱ ሀሳብ የተሰጠበትን እንቅስቃሴዎችን በአብያተክርስቲያናት እቅድ ጋር ማዋሃድ፡፡ ቤተክርስቲያን በሴቶች ላይ የሚደርሰዉን ጥቃት እምቢ ማለት አለባት፡፡

ይህም የዲያቆናት አገልግሎትን በመደገፍ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከቶችን በማስፋፋት፣ቤተክርስቲያንን ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ፣ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ከሚሰሩት መንግስታዊና መንግስታዊ ያለሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በመስራት ነዉ።



## የወል ተጠያቂነትን ለመወጣት የምያግዙ የአሰራር ዘዴዎች

የወል ተጠያቂነትና ለግንኙነት ክፍት መሆን አብሮ ይሄዳሉ። ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን በትክክልና በይፋ ለይቶ የተገነዘቡ ፕሮግራሞችና ድርጅቶች ነበሩ። እነዚህም ጋራዊ የሆነ ተጠያቂነታቸዉን ለመወጣት ሲሰሩ የነበሩ ናቸዉ። የዓለም ሉትራን ፌዴሬሽንም አንዱ ሲሆን ስነ-መለኮታዊ መመሪያዎችን በመከተልም የፆታዊ ጥቃት ድርጊቶችን ይቃወማል፣ ይፋለማልም።

ጋራዊ ተጠያቂነት የተመሰረተዉ በክርስቲያኖች ባለንጀራቸዉን የማገልገል ነጻነት ላይ ነዉ። በሰብአዊ መብት ድንጋጌ እንደተገለጸዉ ማንኛዉም ሰዉ ክብርና ነፃነት አለዉ።

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አገልግሎት በመከተል፣ ቤተክርስቲያን ድሆችን፣ የተጨቆኑትን፣ የተገለሉትንና የተናቁትን በመዉዳድ አፍ እንዲትሆንላቸዉ ተልዕኮ ተሰጥቶአታል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግና ለመደገፍ የዓለም አቀፍ ሰብአዊ ሙብት ሕግን መከተል በጣም ጠቃሚ ነዉ የሚሆነዉ። ቤተክርስቲያንም ተልዕኮዋን ለመወጣት ሁሉም ሰዉ ክብር እንዳለዉ በህብረተሰብ ዉስጥ በሁሉም እንዲታወቅ ማድረግ ይጠበቅባታል።

ሰዎች በሁከትና ብጥብጥ ዉስጥ በሚኖሩበት ሀገሮች ቤተክርስቲያን የዓለም አቀፍ ሰብአዊ ሙብት ሕግን በመደገፍ በዚህ ላይ ጠንክራ መስራት አለባት። በተለይ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን አጥብቃ መቃወምና በዚህም ለተጎዱ ሰዎች ጠበቃና ተሟጋች መሆን ይጠበቅባታል።

ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የሚከተሉትን ማከናወን ያስፈልጋል፡

1. ስለ ዓለም አቀፍ ሰብአዊ ሙብት ሕግ ሰዎች እንዲያዉቁ ማድረግ፣ ይህም የተደነገገዉና የተወሰነዉ በ1325 ጄኔቫ ዉስጥ ነበር።

2. በልማት ዉስጥ ሙብትን መሰረት ባደረገ ሁኔታ ሁሉም ነገር እንዲከናወን ማድረግ፣

3. የሰብአዊ ሙብቶችን መመሪያና ስነ-ምግባር ጉድለት ቅጣት ህግ ማዉጣት፣ይህም በሥልጣን አለ አግባብ መጠቀም፣ ፆታዊ ጥቃት (አስገድዶ መድፈር)፣ እና የመሳሰሉት፣

4. ስነ-ፆታን በተመለከተ ስልጠና መስጠት፣

5. አት ጉዳ የሚለዉን ለመጠቀም ፕሮግራም ማዘጋጀት፣

6. በድርጅትና በፕሮጀክቶች ዉስጥ በንብረት አጠቃቀም ላይ በእኩልነት የመጠቀም ዕድል መፍጠር ናቸዉ።



## መፍትሔ ቃላት

**ፆታ** በህብረተሰብ ዉስጥ የሚታየዉን የስም ወይም የዕድል ልዩነቶችን፣ ይህም ወንድ የመሆንና ሴት የመሆን፣ እንዲሁም የወንድና የሴት ግንኙነቶችን ያመለክታል፡፡ ፆታ በአንድ አዉድ ዉስጥ ከወንድ ወይም ከሴት የሚጠበቀዉን እሴቶችን ይወስናል፡፡

በብዙ ህብረተሰብ ዉስጥ በሃላፊነት ቦታና በየትኛዉም እንቅስቃሴዎች፣ ማለተም በንብረት አጠቃቀምና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነትና መበላለጥ ይታያል፡፡

**የፆታ ትንተና** በየትኛዉም አዉድ የሴቶችና የወንዶች አለመመጣጠን የሚገነዘቡበት መሣሪያ ነዉ፡፡ በተጨማሪም በአንድ አዉድ ዉስጥ ሆኖ ወንዶችም ሴቶችም በተለያየ ሁኔታ መጠቃታቸዉ እምብዛም የሚያስደንቅ ነዉ፡፡

**የፆታ ሚዛናዊነት** በዉክልና እና በተሳትፎ የወንዶችና የሴቶች እኩልነትን ይመለከታል፡፡

**የፆታ እኩልነት** ማለት የወንዶችና የሴቶች፣ ወጣት ወንዶችና ወጣት ሴቶች የመብትና የሃላፊነት እኩልነት ማለት ነዉ፡፡ እኩልነት ማለት ወንዶችና ሴቶች አንድ ናቸዉ ማለት አይደለም፣ ነገር ግን መብታቸዉና ሃላፊነታቸዉ ሴት ወይም ወንድ ሆኖ በመወለዳቸዉ ላይ አይደገፍም፡፡

**የፆታ ትክክለኛነት** ማለት የፆታ እኩልነት የተረጋገጠበት ማለት ነዉ፡፡ ይህም ሴቶችን፣ ልጃገረዶችን፣ ወጣት ወንዶችን እና ወንዶችን እንደየፍላጎታቸዉ በትክከል ማስተናገድን ያሳያል፡፡

**የፆታ ማንነት** አንድ ሰዉ ወንድም ሆነ ሴት፣ ከሌሎች ተለይቶ የሚታወቅበት፣ ራሱን በመግለጽ ማንነቱን የሚገልጽበት ነዉ፡፡ ይህ ወንድ ማን እንደ ሆነና ሴት ማን እንደ ሆነች ይገልጻል፡፡

**የፆታ ፍትህ** በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩትንና የፍጥረታት ባለ አደራዎች የሆኑትን የወንዶችና የሴቶችን ክብር መጠበቅና ማበረታታትን ያመለክታል፡፡ የፆታ ፍትህ የሚገለጸዉ በወንዶችና በሴቶች እኩልነት ነዉ፡፡

**የፆታ ተከታ፡** የወንዶችና የሴቶች የተለየ ፍላጎት፣ ድርሻና ሃላፊነትን በትክክል ማወቅ ነዉ፡፡

**ፆታ** የወንዶችና ሴቶች ተፈጥሯዊ ልዩነትን ያመለክታል፡፡

**ሴቶችን ማሰልጠን**፣በዕዉቀት ማስታጠቅ፤ ሴቶች በተቃራኒ ፆታዎች መካከል ያለዉን ግንኙነት፣ የሴቶች የመስራትና የማስተዳደር ችሎታ የመገንዘብ ለዉጥ ሂደት ነዉ፡፡ በአንድነትና በየግላቸዉ ሴቶች መብታቸዉን መረዳት አሁንም አስፈላጊ ነዉ፡፡




የሉተራ
ዓለም
ፌዴሬሽን
Salem Printing Press
+2519-11220509